## የረቡዕ ህዳር 8 1997ዓ.ም. ( ኖቬምበር 17 2004)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## እረኛዋ ሳይደርስ ላሚቷን ለቅርጫ ፖለቲካ

ባለቤት ያጣች ሀገር በመሆኗ የማንም መጫወቻ ሆና እንዳትቀር አምርረው እየተፋለሙ፥ እየተዋደቁና እየተሰዉ የሚታገሉ ድርጅቶች፥ ለሀገራቸው ያላቸውን ራዕይ፥ ከወያኔ ሌላ ማንም የሚያውቀው እንደሌለ መገንዘብ ይቻላል:: የእነርሱ ራዕይ ከወያኔ እጅግ የተለየ የተቃረነ በመሆኑ፥ እነመለስ ዜናዊ የነዚህን ድርጅቶች ማንነት በሚገባ ማወቃቸው አያስደንቅም:: እሳትና ገለባ፥ አጥፊና ጠፊ፥ መላእክትና ሰይጣን፥ ገዳይና ተገዳይ፥ ሀገር ሻጭና ሀገር አዳኝ፥ ታሪክ አዋራጅና ታሪክ አስከባሪ ወዘተ.. በማንነት ደረጃ መተዋወቃቸው ለዋዛ አይደለም:: ተፃራሪዎች በመሆናቸውም፥ አንዱ የሌላውን አለመኖር አበክረው ይመኛሉ:: ይፈልጋሉ:: ለሀገራዊ አንድነት፥ ለብሔራዊ ጥቅም፥ ለዜጎች አብሮ መኖርና ክብር፥ ለፍትኅ-ርትዕ መቆምና ለጠባብ ዓላማና ለሀገር ጥፋት የቆመ ድርጅት ምንም ቢሆን፥ አይንህን ለአፈር መባባላቸው ያለና ወደፊትም የሚቀጥል ነው:: ለሀገራዊ ጥቅም፥ ለዜጎች አንድነትና ክብር የቆመው ኃይል፥ በአቸናፊነት እስከሚመጣ ድረስ ይህ ክስተት መቆሚያ አይኖረውም:: ይህ ክስተት በትግል እየተሽከረከረ፥ በመሥዋዕት እየታጀበ፥ በቆራጦቹና በአይበገሬዎቹ መራሽነት ግን፥ ዘገየም ፈጠነ መጠናቀቁ አይቀሬ ነው:: ታሪክም ደጋግሞ ደጋግሞ የዚህን ውጤት አስመዝግቦ አቆይቶናል:: አሳይቶናል:: አስተምሮናልም:: ታሪክን ደግሞ፥ ታሪክን አስመዝግቦ፥ ሀገርንና ክብርን ለተተኪው ትውልድ አስረክቦ በክብር የሚያልፈው ፥ ማን እንደሚሆን ወደፊት የሚታይ ሀቅ ነው:: በዚህ ክስተት ብዥታ አይኖረንም:: በየትግሉ ምዕራፍ ሂደት ተንበርካኪዎችና ጨለምተኞች አይኖሩም ማለት ግን አይደለም:: ፖለቲካ ማለት፥ ሊሆን የሚቻለውን የማድረግ ጥበብ ነው የሚባል ዘይ መኖሩን ባንስተውም፥ በመሠረታዊ መርኅ ላይ መደራደር ግን እንዳልሆነ ዕምነታችን የፀና ነው::

መስዋዕት የማይፈልገው ደግሞ፥ ትግል ገና ሳይጀምር የሰለቸው፥ ሦስት ወራት ከአራት ቀናት ማረፊያ ቤት ቀይቶ የወጣው፥ ከጡረታ መልስ እስቲ ዕድሌን በፖለቲካው ልሞክረው የሚለው፥የፖለቲካ አቡጊዳን ሳያውቅ ፕሮፌሰር ሊሆንብን የሚቃጣው፣ በሦስት መንግሥታት የበላው፥ አራተኛው እንዳያመልጠው የሚፈጨረጨረው ወዘተ.. ሁሉ ጆምበሯ ሳትጠልቅበት ሀገሪቱን በሥልጣን ቅርጫ ውስጥ አስገብቶ ለመቀራመት መሞከሩ የሚያስገርም አይደለም:: መለስ ዜናዊ ደግሞ ይህችን አጋጣሚ ላሜ ወለደችልኝ ብሎ እንደሚጠቀምባት አይጠረጠርም:: ይታደሏል እንጅ ይታገሉታል? የሚባለውን ዝባዝ ኪ ተሻምቶ እንደሚናጠቃት የታወቀ ነው:: ይህች የአስራ አንደኛዋ ደቂቃ(ስዓት) የፖለቲካ ሂሳብ (ስሌት)፥ ሀገርን ከጥፋት ለማዳን፥ ሕዝብ እንዳይበጣበጥ ለማድረግ በሚል ሽፋን ለመጠቀም መሞከሩ አያስገርምም:: መንግሥቱ ኃይለማርያም ሀገሪቱን ለወያኔ አጋልጦ ሲሸሽ፥

የኢትዮጵያ ሠራዊት ገትሮ እንዳይወጋና መሳሪያውን አስቀምጦ እጁን እንዲሰጥ በማድረግ÷ ከባዕድ ተባብረው ወያኔ አዲስ አበባ ሰተት ብሎ እንዲገባ የረዱት ሰዎች÷ ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ምን ያህል ተጠልተውና ተዋርደው እንደሚኖሩ እነርሱ እራሳቸው ብቻ ነው የሚያውቁት:: እረኛው ሳይመጣ ሥልጣን ላይ እንውጣ የሚለው ጥድፊያ÷ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን ሳይሆን÷ ሀገሪቱን እንደቅርጫ ለመቀራመት የሚደረግ ሽሚያ ነው:: ለዚህም ይመስላል ዛሬ ÷ በአራቱም ማዕዘናት አዳዲስ የፖሊቲካ ድርጅቶች እየተፈጠሩ ለምርጫ የሚሽቀዳደሙት:: ከቅርጫው ሥጋ ጥቂት ሙዳ ለማግኘት! ይህችን የሥልጣን ጭልፋ( አንጎቻ) ካገኙ ደግሞ÷ እንደተመኘናት÷ ይኸው አገኘናት! እያሉ ጮቤ እንደሚደነክሩ ልንጠራጠር አንችልም::

ይህንን ያዳዲስ ድርጅቶችን በየስርቻው እንደ አሸን ክታብ መፈልፈል÷ መለስና ደንገጡሮቹ ከልብ የሚደግፉበት የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ ስሌት አላቸው:: ፍየል በግርግር እናቷን ታጠቃለች እንደሚባለው÷ ለግርግር ፈጣሪዎች ሙዳ ስጋ በመስጠት÷ ለዳግመኛ ፍሪዳ የቀረበችውን ሀገር÷ ለማጥፋትና የራሳቸውን የተጀመረ የዓላማ ሂደት በሚገባ ለማፋጠንና ከመነሻቸው የጀመሩትን ኅልም ዕውን ለማድረግ ነው:: የሚያሳዝነው ግን÷ ሌላው የአህያ መናጆ በመሆን የአጥፊዎቹ አጫፋሪ የሚሆነው ነው:: : አየ በሬ ሆየ! አየ በሬ ሆየ! ገደሉን ረሳህ ሰርዶውን ስታይ እንደተባለው÷ ሌሎቹ ሁኔታውን የሚመለከቱት ወይም የተረዱት÷ ወያኔ ባዘጋጀው ምርጫ ገብቶ÷ የሰለለ ድምፅ ለማሰማት ይቻላል ከሚለው አንፃር ነው:: ያልተገነዘቡት ጉዳይ ግን÷ በወያኔ ፓርላማ እንኳንስ የሰለለ ድምፅ ቀርቶ÷ እንደ ድመት ቢጳጭሩት÷ እንደውሻ ቢያላዝኑት÷ እንደሜዳ አህያ ቢያናፉት÷ ሰሚ የሌላቸው መሆኑ ነው:: የእነርሱን የሰለለ ድምፅ ማሰማት ደግሞ÷ እነመለስ ዜናዊ በደምብ ይፈልጉታል:: ለምን ቢባል÷ ለባዕዳን ጌቶቻቸው ፍጆታ የሚሆን አቅርቦት ስለሚያገኙበት ነው:: ፓርላማቸው÷ በሚገባ ተከራክሮበት÷ ተፋጭቶበት÷ ተጯጩሆበት÷ ደንክሮበት÷ ጳጭሮበት÷ በሰለለ ጎሮሮው ያሳለፈው የሰለለ ድምፅ ተልካሻ ውሳኔ እንዳለው ሊያሳዩበት ይችላሉ:: ምናልባት ይህንን ዜማ÷ ለሥልጣን ያወጧቸው ባዕዳን ጌቶቻቸው እንደ ሙዚቃ ሊያዳምጡላቸው ይችሉ የሆናል:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ግን÷ መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን ሌላ የሚያመጠው ለውጥ አይኖርም::

ዛሬም እንደትላንቱ÷ መሰረታዊ ለውጥ መጥቶ ነፃ መርጭ እውን እስካልሆነ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ÷ ይህ የመጭው የወያኔ ምርጫ÷ ውጤቱ ምን እንደሚሆን በሚገባ ያውቀዋል:: በመለስ ዜናዊ ድግስ ውስጥ ማን ምን ጉርሻ እንደሚያገኝ ይገነዘበዋል:: እነዚህ የወያኔ ድግስ ዕድምተኞች ለምን እንደተኮለኮሉም ያጤነዋል:: እንዳይሳተፉ የሚፈለጉት ደግሞ በአካባቢው እንዳይቀርቡ የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ እንደማይቆጠቡም በሚገባ ይረዳል:: ወያኔም÷ ይህን በጨረባ ተስካርነት የሚታወቀውን ምርጫ ተሚሙቶ የዴሞክራሲ ጭምብል ለማልበስ እንደሚፍጨረጨር ደህና አድርጎ አውቆበታል:: ግን በዚህም ይወሰድ በዚያ÷ ያው ዞሮ ዞሮ÷ በኢትዮጵያ ብሔራዊና ዘለቄታ ጥቅም ላይ÷ ከነመለስ ዜናዊ ጋር በምንም መንገድ

*ሊደራደር የማይቃጣውን ድርጅት ሆነ ስብስብ ለግቶ ለማስቀረት ነው። ኢትዮጵያ ሐገራችንና ሕዝቧ በዚህ ተፈታታኝና አስተዛዛቢ የታሪክ ወቅት፥ ጥቅማቸውን አሳልፎ የማይሰጥ ድርጅት እንዳላቸው በድጋሜ ያረጋገጡበት ስዓት መሆኑን አውቀውታል። በዘርና በጎጥ የተከፋፈለችን ሀገር ለማዳን የሚታገል ድርጅት፥ ከማህላችን ከገባ ምኞታችን አይፈፀምም፥ያሰናክልብናል ብለው የሚፈሩ ክፍሎች፥ ይህንን ማድረጋቸው ደግሞ የሚያስደንቅ አይሆንም። አንድ አገልጋይ ለሁለት ጌቶች በዕኩልነት ማገልገል ስለሚሳነው፥ አንዱን ትቶ ሌላውን መታዘዝ የግድ ይሆንበታል። በፖለቲካ ሂደት ውስጥም ይሁን፥ በሀገር አድን ትግል ፥ ሁለት የሚጋጩ ዓላማዎችን ማስተናገድ ጭራሽ የሚቻል አይሆንም። የባንዳና የአርበኛ ዓላማና ግብ ምን ጌዜም ተጣጥሞ አያውቅም ። አንዱን ከድቶ ሌላውን መያዝ ግን የመራጩ መብት ነው። ይህንን መብት ደግሞ ማንም ሊነጥቀው አይገባውም። ሌላው ቢቀር፥ ይህንን፤ የወያኔ የዘር ፖለቲካ ያስገኘውን የጎጥ ዴሞክራሲ፥ በየክልሉ እንዲደነክርበት የሚፈቅድለት ይመስለናል። ለሀገራዊ ዓላማ፥ ለብሔራዊ ጥቅም፥ የዜጎቿ እኩልነትና አንድነት ራዕይ ለሚታገል ድርጅት ግን አይሆንም። ይህን ጥብቆ ሳጥልቅህ ቢለውም እንኳ ይጠብበታል። ይተረተርበታል። እየቀደዱ ለመስፋት ደግሞ፥ ጊዜውም ፍላጎቱም የለውም። ጠቀሜታውም አይታየውም። ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ የሚባለውን ይትበኃል ባይስተውም፥ የጠበበን ማስፋት ግን አይከብደውም። ኢትዮጵያን ወደ ቅድመ ቴዎድሮስ ዘመን ለመለወጥ ተግተው ለሚሰሩ ለነመለስ ዜናዊ አባሪ ተባባሪ ሆኖ መገኘት ደግሞ ፥ ኢትዮጵያ እየጠፋች ነው፥ በዘር እየተከፋፈለች ነው፥ ከሚሉት ነባቢታቸው ጋር አብሮ የሚሄድላቸው ሆኖ አልተገኘም። መቸም ሌላ የማናውቀው አዲስ ተአምር ካልመጣ፥ ግመል እየሰረቁ መደበቅ ያስቸግራል።*

*መቸም አውቆ አጥፊ ካልሆነ በቀርና ዕድሌን ከነመለስ ዜናዊ ጋር ባጣምር ይሻለኛል ብሎ የወሰነ ክፍል ካለሆነ በስተቀር፥ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ያስጠብቃልና አብሬው ልሰለፍ ብሎ የሚደራጅ/ የሚታገል ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት አለ ብሎ ማመን ይከብዳል። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ፥ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅላት መንግሥት ያጣችውን ሀገር፥ ጠፍታ ከመጥፋቷ በፊት ለማዳን የሚኖረው፥ምርጫ አንድ ብቻ ነው። ሀገራችንን ማዳን አለብን ብሎ የተነሳውና የቆረጠው ኃይል ተባብሮ በመቆም የኢትዮጵያን አጥፊ አቸንፎ፥ ኢትዮጵያን ማዳን ነው። ሕዝቡም የሚፈልገው ይህንኑ ነው። ይህን ለማወቅ ደግሞ፥ እንደ ሰሎሞን ጥበበኛ፥ እንደ ሳምሶን ጉልበተኛ፥ እንደ መለስ ከዳተኛ፥ እንደ ዳንኤል ኅልም ፈቺ፥ እንደ ቶማስ ተጠራጣሪ፥ እንደ ተፈራ ዋልዋ ተውገርጋሪ፥ እንደ በረከት ስምዖን ቀባጣሪ፥ እንደ ስብሐት ነጋ ክፉ መካሪ፥ እንደ ስዩም መስፍን ፈሪ፥ እንደ ዐባይ ፀሀይ፥ ጠላማይ፥ (ያመኑትን የሚከዳ ማለት ነው በትግርኛ) መሆንን የሚጠይቅ አይመስለንም።*

*ይህ የመንጋዎቹ ጠባቂ ከመምጣቱ በፊት አስቀድምን፥ ተሯሩጠን፥ ተሽቀዳድመን፥ ላሚን ለቅርጫ አቅርበን፥ እንቀራመጣት ዓይነት ጥድፊያ፥*

**በማነኛውም መስፈርት ቢለካ ጤናማ አዕምሮ ያለው ሰው የሚፈጽመው ቀርቶ የሚያስበው ሊሆን አይችልም፡፡ ጅብ ከሚበላህ፥ ጅብ በልተህ ተቀደስ እንደሚባለው፥ እረኛው ከመምጣቱ በፊት ሳሚን ተቀራምተን እንብላ ከተበለ፥ እነርሱም ይቀጥሉ እረኛውም ትግሉን ይቀጥላል፡፡ ኢትዮጵያም በመጨረሻ በጠላቶቿ ላይ ድልን መቀዳጀቷ አይቀሬ ነው፡፡**